**አዋጅ ቁጥር ……/2012**

**የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ወደግል ስለማዛወር የወጣ አዋጅ**

የሀገሪቱን የኢኮኖሚ ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዘላቂነት እንዲኖረው ለማድረግ እና ለግል ኢንቬስትመንት አመቺ የሆነ የፖሊሲ ከባቢዎችን ለመፍጠር የሕግ ማሻሻያዎች ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ለሀገሪቱ የኢኮኖሚ ልማት ስትራተጂ አፈጻጸም አስተዋጽዎ እንዲኖረው ለማድረግ ለልማት የሚውልን የፋይናስ አቅርቦት ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የግል ዘርፉ በኢኮኖሚ ውስጥ የሚኖረውን ሚናና ተሳትፎ ማስፋፋትና ማዳበር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ቅልጥፍና ማሻሻል፣ ተወዳዳሪነታቸውን ማጎልበት፣ ለካፒታል ያላቸውን ተደራሽነት እና የአገልግሎታቸውን ጥራትና ተደራሽነት ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ይህንኑ ዓላማ ከግብ ለማድረስ በሰፊ መሠረት ላይ የተጣለ ይፋና ግልጽ የሆነ የፕራይቬታይዜሽን ፕሮግራም ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ**

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የመንግሥት የልማት ድርጀቶችን ወደ ግል ስለማዛወር የወጣ አዋጅ ቁጥር ……/2012" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፣ በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

1) “ፕራይቬታይዚሽን” ማለት የልማት ድርጅትን ንብረት ወይም አክሲዮኖችን በሙሉ ወይም በከፊል ለግል ዘርፉ በሽያጭ የማስተላፍ ውጤት የሚያስከትል ግብይት ነው፤

2) “የመንግሥት የልማት ድርጅት” ማለት በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 የሚተዳደር የመንግሥት የልማት ድርጅት ነው፤

3) “ቅድመ ፕራይቬታይዜሽን ሥራዎች” ማለት በሚኒስቴሩ የሚከናወን የልማት ድርጅትን ንብረት ወይም አክሲዮኖችን በሙሉ ወይም በከፊል ወደ ግል ለማዛወር የታቀደ ማናቸውም ዝግጅት ወይም ሂደት ነው፤

4) “ወርቃማ አክሲዮን“ ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የመንግሥት የልማት ድርጅትን በመለወጥ የካፒታሉ አካል የሆነና በማናቸውም የቦርድ ውሳኔ ላይ ድምፅ የመስጠትና ድምፅን በድምፅ የመሻር መብቶችን ለመንግሥት የሚያጎናጽፍ በአክሲዮን መመስረቻ ፅሁፍ ውስጥ የተደነገጉ ልዩ መብቶችን የያዘ አክሲዮን ነው፤

5) “ኤጀንሲ” ማለት የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ ነው፤

6) “ሚኒስቴር” እና “ሚኒስትር” ማለት እንደቅደምተከተሉ የገንዘብ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

7) “ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን” ማለት ኤጀንሲውን ጨምሮ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984መሠረት የመንግሥት የባለቤትነት መብቶችን ለመከታተል፣ ለመጠበቅ፣ ለመተግበር በሚኒስትሮች ምክር ቤት የተሰየመ ባለሥልጣን ነው፤

8) “ባለአደራ” ማለት በሚኒስቴሩ ሥር የተደራጀ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ነው፡፡

9) “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

10) ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ፆታ ይጨምራል፡፡

3. <u>የፕራይቬታይዜሽን ዓላማዎች</u>

የፕራይቬታይዜሽን ፕሮግራም የሀገሪቱን የኢኮኖሚ ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን የሚደግፍ በግልፅነት፣ በአሳታፊነትና በተዓማኒነት መርሆዎች ላይ ተመሥርቶ የሚከናወን ሲሆን የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፤

1) የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ውጤታማነትን ማሻሻል፣ ተወዳዳሪነታቸውን ማጎልበት፣ የቴክኒክ ሙያንና ክህሎትን መጋበዝ እና የካፒታል አቅርቦትን ማሻሻል፤
2) መንግሥት የሚያካሂዳቸውን የፋይናንስ እንቅስቃሴዎች ለማጎልበት ገቢዎችን ማሰባሰብና የልማት ፋይናንስ አቅርቦትን ማጎልበት፤
3) ለግል ኢንቬስትመንት የፖሊሲ ከባቢዎችን በማጎልበትና የግል ዘርፉን መስፋፋት በማበረታት የሀገሪቱን የኢኮኖሚ ልማት ማሳደግ፡፡

## ክፍል ሁለት

## <u>ስለቅድመ ፕራይቬታይዚሽን ሥራዎች</u>

4. <u>ለቅድመ ፕራይቬታይዜሽን ሥራዎች የተለያዩ አካላት ኃላፊነት</u>

1) የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚኒስቴሩን እና የተቆጣጣሪውን ባለሥልጣን የውሳኔ ሃሣብ ከግምት ውስጥ በማስገባት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ወደ ግል መዞር ያለበትን የልማት ድርጅት ይወሰናል፡፡
2) ሚኒስቴሩ፡-

   ሀ. ማናቸውንም የቅድመ ፕራይቬታይዜሽን ሥራዎች የሚያከናውን ሲሆን የሚመለከተውን የመንግሥት የልማት ድርጅት ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን በማማከር የቅድመ ፕራይቬታይዜሽን ሂደት መቼ መጀመር እንዳለበትና የትኞቹ ሥራዎችም መካተት እንዳለባቸው፣

   ለ. ከመንግሥት የልማት ድርጅት ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ጋር በመካከር የእያንዳንዱን ሽያጭ አመላካች የሽያጭ ዋጋ (ወይም መነሻና መድረሻ ዋጋ) እና ወደ ግል የሚዛወረውን የአክሲዮን መጠንን (የድርጅቱን መጠንን)፣

   ሐ. የመንግሥት የልማት ድርጅት ዋጋ ግምትን፣ እንደገና የማዋቀር ጥረቶች ውጤቶችን፣ ወቅታዊው የገበያ ሁኔታዎችን እና ድርጅቱ ኢንቬስተሮችን መሳብ

የመቻሉን ዕድል ከግምት ውስጥ በማስገባት እያንዳንዱ የመንግሥት የልማት ድርጅት ወደ ግል ለመዛወር ያለውን ዝግጁነት፣

ይወስናል፡፡

3) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግሥት የልማት ድርጅቱ ለፕራይቬታይዜሽን ዝግጁ መሆኑ ታምኖ የፕራይቬታይዜሽን ስልቱ ሲወሰን ኤጀንሲው ፕራይቬታይዜሽኑን የመተግበር እንቅስቃሴ ይጀምራል፡፡
4) ወደ ግል የሚዛወር የልማት ድርጅት የሥራ አመራር ቦርድ፤

(ሀ)ከሚኒስቴሩ እና ከተቆጣጣሪው ባለሥልጣን በሚቀርብለት ጥያቄ መሠረት የመንግሥት የልማት ድርጅቱን በሚመለከት የተሟላ መረጃ ይሰጣል፤

(ለ) ከተቆጣጣሪው ባለሥልጣን ጋር በመመካከር በሚኒስቴሩ በተሰጡት መመሪያዎች መሠረት የመንግሥት የልማት ድርጅቱን ለቅድመ ፕራይቬታይዜሽንና ለፕራይቬታይዜሽን ያዘጋጃል፤

(ሐ) በቅድመ ፕራይቬታይዜሽን ሂደትና በፕራይቬታይዜሽን ወቅት የልማት ድርጅቱ ንብረት ዋጋ እያሽቀለቆለ አለመሄዱንና ለብክነት አለመዳረጉን ያረጋግጣል፤

(መ)በመደበኛው የንግድ እንቅስቃሴ ምክንያት ወይም በሚኒስቴሩ ስምምነት ካልሆነ በቀር፣ በቅድመ ፕራይቬታይዜሽን ወቅትና በፕራይቬታይዜሽን ደረጃ ማናቸውም አዲስ ኢንቬስትመንት ከማድረግ መቆጠብ ይኖርበታል፡፡

5. <u>በቅድመ ፕራይቬታይዜሽን የመንግሥት የልማት ድርጅትን እንደገና ስለማዋቀርና ሌሎች ተግባሮች</u>

1) ሚኒስቴሩ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) መሠረት ከተቆጣጣሪው ባለሥልጣን ጋር በመቀናጀት የልማት ድርጅቱ ወደ ግል ከመዛወሩ በፊት ተገቢው የካፒታል አደረጃጀቶች፣ የንግድ ስትራቴጂ፣ የኮርፖሬት አስተዳዳር መዋቅሮች እና የሪፖርት አቀራረብና የመረጃ አገላለጽ ልምዶች ያለው መሆኑን ይገመግማል፤ ጉድለት በሚኖርበትም ጊዜ አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፡፡
2) ተቆጣጣሪው ባለሥልጣን የሚኒስቴሩን የቅድመ ፕራይቬታይዜሽን እንቅስቃሴን ለመደገፍ በመንግሥት የልማት ድርጅቱ ላይ ክትትል ባደረገበት ወቅት ያደረጋቸውን

ማናቸውንም የኦፕሬሽን ግምገማዎችንና ተዛማጅ መረጃዎችን ለሚኒስቴሩ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

3) ሚኒስቴሩ አስፈላጊ የሆኑ ማናቸውም የኦፕሬሽንና የፋይናንስ ሥርዓትን እንደገና የማዋቀር ኃላፊነት አለበት፤ ወደ ግል ከመዛወሩ በፊትም እንደገና መዋቀሩ የመንግሥት የልማት ድርጅቱን ዋጋና ተፈላጊነቱን የሚያሳድግ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

4) ሚኒስቴሩ ከፕራይቬታይዜሽን በኋላ ተገቢ ያልሆነ የውድድር ባህርያት፣ የገበያ ልምዶች እና መጠኑ ያለፈ የገበያ የበላይነት እንዳይከሰት በፕራይቬታይዜሽን ደረጃ ወይም ወቅት በሥራ ላይ ባለው ሕግ መሠረት አስፈላጊውን እርምጃ ሁሉ ይወስዳል፡፡

## 6. <u>የመንግሥት የልማት ድርጅትን ወደ አክሲዮን ማኅበርነት ስለመለወጥ</u>

1) የንግድ ሕግ አንቀጽ 307(1) ቢኖርም፣ አንድን የመንግሥት የልማት ድርጅትን ለፕራይቬታይዘሽን ዝግጁ ለማድረግ በአንድ ባለአክሲዮን ባለቤትነት ወደሚያዝ የአክሲዮን ማኅበርነት ሊለወጥ ይችላል፡፡

2) የልማት ድርጅቱ ወደ አክሲዮን ማኅበርነት በሚለወጥበት ወቅት አክሲዮኖቹ ወደ ግል ባለቤትነት እስከሚዛወሩ ድረስ የድርጅቱ ካፒታል በአክሲዮኖች ተከፋፍሎ አክሲዮኖቹ በመንግሥት ይያዛሉ፡፡

3) በንግድ ሕጉ ለባለአክሲዮኖች ጉባዔ የተሰጡ ሥልጣኖች በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ መሠረት አግባብነት ላለው የመንግሥት የልማት ድርጅት ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን እንደተሰጡ ይቆጠራሉ፡፡

4) ከንግድ ሕጉ አንቀጽ 307 ንዑስ አንቀጽ (1)፣ አንቀጽ 311፣ አንቀጽ 347 ንዑስ አንቀጽ (1) እና አንቀጽ 349 በስተቀር ሌሎቹ የንግድ ሕግ ድጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

5) በንግድ ሕጉ አንቀጽ 546 ከንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (4) እና በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 69 (1) እና (2) የተደነገጉት ቢኖሩም፣ ሚኒስቴሩ የመንግሥት የልማት ድርጅትን ወደ አክስዮን ማኅበርነት በሚለውጥበት ጊዜ ለአክሲዮን ማኅበሩ የሚተላለፉትን የመንግሥት የልማት ድርጅቱን ሀብትና ዕዳዎች እንዲሁም ንብረቶቹ እንደገና ከተገመቱ በኋላ ካፒታሉን የመወሰንና የማሳደግ ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

6) ወደ አክሲዮን ማኅበርነት የተለወጠ የመንግሥት የልማት ድርጅት እንደተመዘገበ ህልውናው ያከትማል፡፡

7. <u>የመንግሥት የልማት ድርጅቱን ዋጋ ስለመተመን</u>

1) ሚኒስቴሩ የልማት ድርጅትን፣ የልማት ድርጅትን የተወሰነ ክፍል ወይም ንብረት ወይም የመንግሥት አክሲዮንን ወደ ግል ለማዛወር በቅድሚያ ዋጋው ገለልተኛ በሆነ ብቃት ባለው ባለሙያ እንዲተመን ማስደረግ አለበት፡፡

2) የዋጋ ትመናው የሚከናወነው በሚኒስቴሩ ቁጥጥር ሥር የሚደረገው የልማት ድርጅቱን የፋይናንስ እና/ወይም የኦፐሬሽን እንደገና የማደራጀት ሥራ መጠናቀቅ ተከትሎ ሚኒስቴሩ ባወጣው የዋጋ ትመና መመሪያ መሰረት ይሆናል፡፡

3) በዋጋ ትመናው መሰረት የሚወሰነው የመሸጫ መነሻ ወይም አመልካች ዋጋ በፕራይቬታይዚሽኑ ሂደት በኤጀንሲው ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት በሚኒስቴሩ መጽደቅ አለበት፡፡

## ክፍል ሦስት

## <u>የፕራይቬታይዚሽን አፈጻጸም ማዕቀፍ</u>

8. <u>የፕራይቬታይዜሽን አፈጻጸም</u>

1) የሚኒስትሮች ምክር ቤት የፕራይቬታይዜሽን አፈጻጸምን በተመለከተ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

(ሀ) ከኤጀንሲው ውጭ ላለ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ተጠሪ የሆነን የመንግሥት የልማት ድርጅት ወይም በተቆጣጣሪ ባለሥልጣን የተያዙ አክሲዮኖች ወደ ግል ማዛወሩ ከመከናወኑ በፊት ለኤጀንሲው መተላለፋቸውን ያፀድቃል፤

(ለ) የሚኒስቴሩንና የኤጀንሲውን የውሳኔ ሀሳብ ከግምት ውስጥ በማስገባት የማናቸውም ወርቃማ አክሲዮን አጠቃቀም፣መዋቅር እና አተገባበሩን ያፀድቃል፤

2) ኤጀንሲው የፕራይቬታይዘሽንን አፈጻጸም በተመለከተ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፤

(ሀ) የሽያጭ ማከናወኛ ሥነ ሥርዓቶችን ያዘጋጃል፤

(ለ) ለእያንዳንዱ ሽያጭ የሚያገለግል የጨረታ መመዘኛ መስፈርቶችን ይወስናል፤

(ሐ) የመሸጫያ ጊዜን ይወስናል፣እያንዳንዱን ሽያጭ ያማቻቻል፣ ሽያጩን በበላይነት ይከታተላል፤

(መ) ሽያጭ ሲከናወን የሚያግዙ ባለሙያዎችን ይቀጥራል፤

(ሠ) ፍላጎት ያላቸው ኢንቬስተሮች በግዢው እንዲሳተፉ ከበቂ ጊዜ ጋር ሽያጩን በሕዝብ መገናኛ ያሳውቃል፤

(ረ) አስፈላጊውን ሰነዶችና ናሙና ውሎችን ያዘጋጃል፤

(ሰ) በማናቸውም ድህረ ፕራይቬታይዜሽን ኢንቬስትመንት መስፈርቶች ላይ ውሳኔ ይሰጣል፤

(ሸ) ማንኛውም ባለሀብት በረዥም ጊዜ በሚፈጸም ክፍያ የሽያጩን ዋጋ የመክፈል መብት የሚሰጠው መሆን አለመሆኑን እና ክፍያ የሚፈጸምበትን ሕጋዊ ገንዘብ ይወስናል፤

(ቀ) የፕራይቬታይዜሽን ሂደት አተገባበሩ ሥርዓት ያለው፣ ሕጋዊ፣ግልጽና ቀልጣፋ መሆኑን ያረጋግጣል፤

(በ) ከፕሮግራሙ አፈጻጸም ጋር በተያያዙ የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ እንደአግባቡ ለመንግሥት የውሳኔ ሃሣብ ያቀርባል፤

(ተ) ከሕዝብ ጋር ግንኙነት ይፈጥራል፣ የፕራይቬታይዜሽን ፕሮግራም እንቅስቃሴዎችን ወይም ክንዋኔዎችን ያስተዋውቃል፡፡

3) የመንግሥት የልማት ድርጅት ለፕራይቬታይዘሽን ዝግጁ መሆኑ ከተረጋገጠ እና የፕራይቬታይዜሽን ስልቱ በሚኒስቴሩ ሲወሰን ኤጀንሲው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ከንዑስ አንቀጽ (2) እስከ (4) በተደነገገው መሠረት ለዚሁ ባቋቋመው ክፍል አማካይነት ወደ ግል የማዛወሩን ተግባር ማከናወን ይጀምራል፡፡

4) ኤጀንሲው ከሚኒስቴሩ ጋር በመቀናጀት የመሸጪያ መነሻ ዋጋ ወይም በግብይት ወይም በንግድ ላይ የተመሠረተ ተመሳሳይ ዋጋ ወይም በውድድር ላይ የተመሠረተ ጨረታ ወይም በጨረታ ላይ የተመሠረተ ተመሳሳይ ሽያጭ ከመጀመሩ ቀድም ብሎ የሚቀርበውን የመጨረሻውን የሽያጭ መጠንን እና የአክሲዮን ዋጋን ይወስናል፤

5) ኤጀንሲው ፕራይቬታይዜሽንን፣ ለሽያጭ የሚቀርበውን የአክሲዮን ዋጋን ወይም መጠንን ወይም የልማት ድርጅቱን ድርሻ በተመለከተ የቀረበውን ሀሳብ በገበያው፣ በዘርፉ ሁኔታዎች ወይም በሌሎች ምክንያቶች መቀያየር ማሻሻል የሚያስፈልግ ሆኖ ከተገኘ ለሚኒስቴሩ መልሶ ያሳውቃል፤

6) የመንግሥት የልማት ድርጅትን ወደ ግል ማዛወር ያልተቻለ እንደሆነ ተቆጣጣሪው ባለሥልጣን አግባብ ባላቸው የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ሕግ መሠረት ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ጥያቄ አቅርቦ ሲፀድቅለት የመንግሥት የልማት ድርጅቱ ሊፈርስ ይችላል፡፡

## ክፍል አራት

## የፕራይቬታይዜሽን ስልቶች

### 9. የፕራይቬታይዜሽን ስልቶች

1) በሥራ ላይ የሚውል ማናቸውም የፕራይቬታይዜሽን ስልት አተገባበር በግልጽነት መርሆዎች ላይ የተመሠረተ እና ግቡም ለመንግሥት ተስማሚ የሆኑ ስምምነቶች ላይ መድረስ ነው፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ከዚህ በታች ከተመለከቱት የፕራይቬታይዜሽን ስልቶች አንዱ እንደአግባቡ ተፈጻሚ ሊሆን ይችላል፤

(ሀ) በውድድር ላይ በተመሠረተ ጨረታ፤

(ለ) ለሕዝብ ክፍት በሆነ ጨረታ፤

(ሐ) የአክሲዮን ገበያ ወይም ሌሎች ተስማሚ የግብይት መድረኮች ያሉ እንደሆነ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ለሕዝብ ለሽያጭ በሚቀርብ አክሲዮን፤

(መ) በረዥም ጊዜ ተከፋፍሎ በሚሸጥ የተሰበጣጠረ ግዢ፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ኤጀንሲው በሚኒስቴሩ ፈቃድ ተስማሚና ለኢንዱስትሪው ደረጃ የሚመጥን የንግድ ወይም የስትራቴጂክ ሽያጭን በቅድሚያ በተመረጡ አነስተኛ ቁጥር ባላቸው የኮርፖሬት ኢንቬስተሮች ላይ ያነጣጠረ ሽያጮችን የመሳሰሉ ሌሎች የፕራይቬታይዜሽን ስልቶችን መምረጥ ይችላል፡፡

4) የፕራይቬታይዜሽን ስልቶች በተመለከተ የተደነገገው ቢኖርም፣ ሚኒስቴሩ ከኤጀንሲው ጋር በመመካከር ከሚሸጡት አክሲዮኖች ውስጥ የተወሰኑት በመንግሥት የልማት

ድርጅቱ ሠራተኞች ተለይተው የሚያዙበትን ሁኔታ እና የአክሲዮኖቹን ዋጋና መጠን ይወስናል፡፡

5) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የፕራይቬታይዜሽን ሽያጭ የመንግሥትን አክሲዮኖች መቶ በመቶ ወይም ከፊሉን ሊያካትት ይችላል፡፡

6) አብላጫውን ወይም ወሳኝ የሆኑ አክሲዮኖችን ሽያጭ በሚመለከት መንግሥት ወርቃማውን አክሲዮን ማስቀረትን መምረጥ ይችላል፡፡ ወርቃማ አክሲዮን መንግሥት የሕዝብ ጥቅምን አያስጠብቅም ብሎ ባመነበትን በማናቸውንም የቦርድ ውሳኔ ላይ ድምፅ የመስጠትና ድምፅን በድምጽ የመሻር መብት ያጎናጽፈዋል፡፡

7) የፍታብሔር ሕግ አንቀጽ 1750 ድንጋጌ ቢኖርም፣ የመንግሥት የልማት ድርጅቱ የሽያጭ ዋጋ የሚከፈለው በውሉ በተመለከተው ሕጋዊ ገንዘብ ይሆናል፡፡

## ክፍል አምስት

## <u>ድህረ ፕራይቬታይዜሽን ታሳቢዎችና ግምገማዎች</u>

### 10. <u>ድህረ ፕራይቬታይዜሽን የኢንቬስትመንት ታሳቢዎች እና ግምገማዎች</u>

1) የድህረ ፕራይቬታይዜሽን የኢንቬስትመንት ግዴታዎች የፕራይቬታይዜሽን ውሉ አካል ሊሆኑ ይችላሉ፡፡
2) የልማት ድርጅት ገዢ በውሉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ እና በሽያጭ ውሉ በተደረሰው ስምምነት መሠረት ማናቸውንም ድህረ ፕራይቬታይዜሽን ኢንቬስትመንት የመፈጸም ግዴታ አለበት፡፡
3) ኤጀንሲው የድህረ ፕራይቬታይዜሽን ግዴታዎችን አፈጻጸምን ይከታተላል፡፡
4) ባለሀብቱ የውል ግዴታዎችን ለመከታተል የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ለኤጀንሲው በየጊዜው የማቅረብ እና የኤጀንሲው ተወካዮች ቅድመ ዝግጅት በማድረግ በማናቸውም ጊዜ ወደ ተሸጠው የልማት ድርጅት እንዲገቡና ግምገማ እንዲያከሂዱ የመፍቀድ ግዴታ አለበት፡፡

### 11. <u>ድህረ ፕራይቬታይዜሽን ግምገማ</u>

1) ኤጀንሲው በፕራይቬታይዜሽን ክንውኑ ላይ ግምገማ የሚያካሂድ ገለልተኛ ባለሙያ በመሾም በግኝቶቹ ላይ ዓመታዊ ሪፖርት ማውጣት ይኖርበታል፡፡

2) የግምገማው ሪፖርት የተላለፉና ቀሪ የሆኑ ወይም የተከፈሉ የመንግሥት ዕዳዎችን፣ የመንግሥት ዋስትናዎች ያሉበትን ደረጃና ሌሎች ተያያዥ ዕዳዎችን፣ ወደ ግል በተዛወረው የመንግሥት የልማት ድርጅት የመንግሥት ገንዘብ ያለመኖር ያስከተለውን ተፅህኖ ወይም ውጤቶች፣ በግል ዘርፉ የተመዘገበውን ውጤታማነት መገምገም ይኖርበታል፡፡ እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች የግምገማ መለኪያዎችን ማካተት ይኖርበታል፡፡

## 12. <u>ስለ ልማት ድርጅቶች መብትና ግዴታ መተላለፍ</u>

1) ወደ ግል የተዛወረ የመንግሥት የልማት ድርጅት በአክሲዮን ማኅበርነት እንደተመዘገበ ህልውናውን ያጣል፡፡ የመንግሥት የልማት ድርጅቱ መብቶችና ግዴታዎች በሽያጭ ውሉ መሠረት ለገዢው መተላለፍ ይኖርባቸዋል፡፡

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም፣ ተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሣቦች ወደ ገዢው እንደማይተላለፉ በሽያጭ ወሉ ውስጥ ስምምነት ከተደረገ ከዚሁ ጋር የተያያዙ መብትና ግዴታዎች ወደ ባለአደራ ይተላለፋሉ፡፡

3) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (5) መሠረት ከሚኒስቴሩ ውሳኔ በኋላ ወደ አክሲዮን ማኅበርነት ወደ ተለወጠው የመንግሥት የልማት ድርጅት ከተላለፉት ሀብትና ዕዳዎች ላይ ዕዳቸው ተከፍሎ የቀሩ ንብረትና ዕዳዎች ወደ ባለአደራ መተላፍ ይኖርባቸዋል፡፡

4) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ድንጋጌዎች በአዋጅ ቁጥር 110/1987 መሠረት በኤጀንሲው በተሰጠ ውሳኔ ለቀድሞው ባለንብረቶች ለተመለሱ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የሚተላለፉ መብትና ግዴታዎችን በተመለከተ በተመሳሳይ ሁኔታ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

5) የመንግሥት የልማት ድርጅት ወደ ግል ከመዛወሩ በፊት የነበረ የጡረታ ሽፋን ሳይቋረጥ ይቀጥላል፡፡ የአዲሱ ድርጅት ባለቤት የሠራኞችን ጡረታ በተመለከተ አግባብ ባላቸው ሕጎች በአሠሪዎች ላይ የተጣሉትን ግዴታዎች ማክበር ይኖርበታል፡፡

## 13. <u>አለመግባባትን ስለመፍታት</u>

1) በውላቸው ውስጥ በግልጽ በተመለከተ የግልግል ዳኝነት ሂደት ወይም አካል እንዲታይ የተስማሙ ካልሆነ በስተቀር፣ በኤጀንሲውና በመንግሥት የልማት ድርጅት ገዢ መካከል የሚነሳ ክርክር የሚቀርበው ሥልጣን ላለው የፌዴራል ፍርድ ቤት ይሆናል፡፡
2) ተዋዋይ ወገኖች ክርክራቸው በግልግል ዳኝነት አካል እንዲታይ የተስማሙ ከሆነ፣ የግልግል ሂደቱ በውሉና አግባብ ባላቸው የፍትሐብሔር ሕግና የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ይመራል ፡፡

14. <u>ስለታክስ</u>

1) ታክስ የሚያርፍባቸውን ገቢዎች መወሰንን በተመለከተ የንብረት የእርጅና ቅናሽ ስሌት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 መሠረት በተደረገው የልማት ድርጅቶች ዋጋ ግምት ላይ የተመሠረተ ይሆናል፡፡ ሆኖም የጨረታው ዋጋ አነስተኛ ከሆነ ገዢው በከፈለው ትክክለኛ ገንዘብ ላይ የተመሠረተ ይሆናል፡፡
2) ኤጀንሲው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተወሰነውን የንብረቶቹን ዋጋ ዝርዝር ለሚመለከተው የታክስ ባለሥልጣን ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
3) ኤጀንሲው ከንብረት ባለቤትነት ሰነድ ጋር በተያያዘ የቀረጥ ቴምብር የተከፈለባቸውን ለገዢው የተላለፉ ንብረቶች ዋጋ ዝርዝርንም ለሚመለከተው የታክስ ባለሥልጣን ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

## ክፍል ስድስት

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

15. <u>ከፕራይቬታይዜሽን የተገኘ ገንዘብን ስለመጠቀም</u>

ከፕራይቬታይዜሽን ከተገኘ ገንዘብ ላይ ለክንውኑ የተደረገው ወጪ ተቀንሶ ቀሪው ገንዘብ ሚኒስቴሩ በሚያስተዳድረው የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ የባንክ ሂሣብ ተቀማጭ ይደረጋል፡፡

16. <u>የመተባበር ግዴታ እና የኤጀንሲው ኃላፊነት</u>

1) ማንኛውም የፌዴራል ወይም የክልል መንግሥት አካል ወይም የመንግሥት ባለሥልጣን የፕራይቬታይዜሽን ፕሮግራሙን በማስፈጸም ሂደት የሚጠየቀውን መረጃ ወይም ድጋፍ በመስጠት የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ለኤጀንሲው የሚተላለፉ መረጃዎችና ለገዢዎች የሚሰጡ አገልግሎቶች የሚቀርቡበት የጊዜ ገደብ በኤጀንሲው ይወሰናል፡፡

3) ከባለቤትነት ማስረጃዎች፣ ከአገልግሎት ውሎች እና ከንግድ ፈቃዶች ዝውውር ጋር በተያያዘ ገዥው ፎርማሊቲዎችን ለሟሟላት የሚያጠፋው ጊዜ የጊዜ ገደቡን ለማስላት ታሳቢ አይሆንም፡፡

17. <u>ሕገወጥ ባለይዞታዎችን ስለማስለቀቅ</u>

1) ወደ ግል እንዲዛወር የተደረገ የልማት ድርጅት ሕንፃን ወይም ቅጥር ግቢን በሕገወጥ መንገድ በመያዝ ርክክብ እንዳይፈጸም ያወከ ሰውን ለማስለቀቅ የክስ አቤቱታ የቀረበለት ፍርድ ቤት የይዞታውን ሕጋዊነት የሚያሳይ መከላከያ ካልቀረበለት በስተቀር በ30 (ሰላሣ) ቀናት ውስጥ የማስለቀቂያ ትእዛዝ በመስጠት ውሳኔውን ያስፈጽማል፡፡

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ከአዋጅ ውጭ ስለተወሰዱ ንብረቶች በወጣው አዋጅ ቁጥር 110/1987 መሠረት በኤጀንሲው ውሳኔ ለቀድሞ ባለቤቶቻቸው በሚመለሱ ንብረቶችም ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ ሆኖም የይዞታውን ሕጋዊነት የሚመለከት መከላከያ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

18. <u>የተሻሩና ተፈጻሚ የማይሆኑ ሕጐች</u>

1) የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ወደ ግል ለማዛወር የወጣው አዋጅ ቁጥር 146/1991 (እንደተሻሻለ) በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

2) ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ደንብ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

19. <u>ተፈጻሚነት ያለው ሕግ</u>

1) ነባር ድርጅትን ለማስፋፋትና ለማሻሻል ስለሚሰጡ ማበረታቻዎች እንዲሁም የውጭ ዜጎችና ባለሀብቶች በኢንቨስትመንት መስክ ስለሚሳተፉበት ሁኔታ ስለሚጠበቁላቸው መብቶች አግባብነት ባላቸው ኢንቨስትመንት ሕጎች የተደነገጉት የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ወደ ግል በተዛወረላቸው ላይም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም፣ በኢንቬስትመንት ሕጉ ለሀገር ውስጥ ባለሀብት የተሰጠው ትርጉም ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም መንግሥትንና የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን አይጨምርም፡፡

20. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከ……….ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ …….. ቀን 2012 ዓ.ም

*ሳህለወርቅ ዘውዴ*
*የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሳዊ*
*ሪፐብሊክ ፕሬዝዳንት*